# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 159 ግንቦት 25 2003 ገጽ 1

> የወያኔ ዘረፋ “የህግ” ሽፋን ያለው በመሆኑ በቀላሉ ላይታይ ይችላል። “መሬት አይሸጥም” ሲል ለድሃው ያሰበ ይመስል ይሆናል። እሱ ግን ይሸጣል። መንገድና ድልድይ፤ ግድብና መስኖ የመሳሰሉ ግንባታዎችም ሹማምንቱ ለሚያገኙት ጉርሻ ሲሉ የሚሯሯጡላቸው ነገሮች ናቸው። የባንክ ብድርም ስውር መዝረፊያቸው ነው። እርዳታ የተለመደ መክበሪያቸው ነው።
>
> ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

### የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አመጹ፣ የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ፌደራል ፖሊሶች ተማሪዎችን ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ጨፈጨፉ

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች “ከፍላጎታችን ውጭ ተገድደን ለአባይ ግድብ ስራ የምንበላውን ምግብ አንነጠቅም በማለት ተቃዉሞ በማሰማታቸው በርካታ የፌደራል ፖሊሶች በቦታው በመድረስ ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ተማሪዎችን ሲደበድቡ መዋላቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአርባምንጭ ከላከልን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል። በዚህ ጭካኔ በተሞላበት ድብደባ የሞቱና ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ ተማሪዎች እንደሚገኙበት ዘጋቢያችን በተጨማሪ ከስፍራዉ ካስተላለፈልን ዜና ለማወቅ ተችሏል። እንደ ሪፖርተራችን ዘገባ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ትምህርት ያቆሙ ሲሆን በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ የተፈጠረው ውጥረት አሁንም እንዳልበረደ ለማወቅ ተችሏል።

1. ለዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ ያደሩ የዩኒቨርሲቲው ባለስልጣናት ተማሪዎችን ያለፍላጎታቸውና ያለፈቃዳቸው ከሚመገቡት ምግብ ላይ ለአባይ ግድብ ስራ እገዛ ተቀናሽ እንዲሆን ማድረጋቸው የተማሪዎችን ቁጣ ከመቼዉም በላይ መቀስቀሱ ታውቋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

### መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ የዘረፉት 8.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የአገራችንን ድህነት ለመቅረፍ የሚያስችል በርካታ የልማት ግንባታዎችን ሊያሰራ የሚችል ነው ተባለ

ዩ ኤን ዲ ፒ የተባለው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም በመለስ ዜናዊ የሚመራው የወያኔ ሹማምንት በህገወጥ መንገድ ከአገር አሸሽተዋል ያለው 8 ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወይም በአገራችን ገንዘብ ሲሰላ አንድ መቶ ሃምሳ ቢሊዮን ብር በላይ የሆነ ጥሬ ገንዘብ ወደ አገር ቢመለስ በርካታ የልማት ተግባራትን ማከናወን የሚችል እንደሆነ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ለሚዲያ ባሰራጩት ጥናታዊ ጽሁፋቸው ገለጹ።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁንጮዎችና ጀሌዎቻቸው ከሃያ ዓመታት በፊት አዲስ አበባ ሲገቡ ተቀያሪ ጫማ እንዳልነበራቸዉ የገለጹት አቶ ኤፍሬም ዛሬ ያ ሁሉ ተዘንግቶ እነሱና ልጆቻቸዉ የሚለብሱት ልብስና የሚጫሙት ጫማ በተላላኪ ከሮምና ከፓሪስና በከፍተኛ የህዝብ ገንዘብ እንደሚገዛ ገልጸዋል። በመቀጠልም ይህ ነዉ የሚባል የባንክ ሂሳብ ያልነበራቸዉ የወያኔ ሹማምንት ዛሬ የነሱ፤ ቤተሰቦቻቸዉና የቅርብና የሩቅ ዘመዶቻቸዉ ገንዘብ የአዉሮፓንና የኤሲያን ትላልቅ ባንኮች እንዳጣበበዉ ከአቶ ኤፍሬም ጥናታዊ ጽሁፍ ማወቅ ተችሏል።

አቶ ኤፍሬም ማዴቦ በዚሁ ጥናታዊ ጽሁፋቸው የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከኢትዮጵያዊያን በመዝረፍ በውጪ ሃገራት ያከማቸው 8 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ወደ አገር ቤት ቢመለስ በአሁኑ ሰዓት ለህዳሴዉ ግድብ ግድብ ማሰሪያ ገንዘብ አዋጣ እያሉ ህዝቡን በቁም ስቅሉን ከሚያሳዩት በግማሹ ገንዘብ ብቻ ግድቡን ገንብተዉ በተቀረው ገንዘብ የጥራት ደረጃቸውን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

### የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት አሁን ካለበት 7.5 በመቶ ወደ 6 በመቶ ይወርዳል ተባለ፣ የዘረኛው ወያኔ የሁለት አሃዝ እድገት ዲስኩር ውድቅ ሆነ

አይ ኤም ኤፍ በመባል የሚታወቀው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም በያዝነው የ2011 ዓም በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የ 7.5 በመቶ እድገት በሚቀጥለው 2012 ዓም ወደ 6 በመቶ እንደሚወርድ መተንበዩን ሮይተርስና ብሉምበርግ በመባል የሚታወቀዉ አቢይ የዜና አውታር በየግላቸዉ ባወጡት ዘገባ ገለጹ።

እንደ ብሉምበርግና ሮይተርስ ዘገባ አይ ኤም ኤፍ እዚህ ትንበያ ላይ ሊደርስ የቻለዉ በሃገሪቱ እየታየ ያለው ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት፣ በግል ባንኮች ብድር አሰጣጥ ላይ ዘረኛው አገዛዝ የጣለው ገደብ፣ እንዲሁም ከንግድ ስራ ጋር በተያያዘ በሃገሪቱ ከሚታየው እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ በመነሳት መሆኑ ታውቋል። ይህ አይ ኤም ኤፍ ይፋ ያደረገዉ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት መጠን መረጃ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እያስመዘገብሁ ነው ከሚለው የሁለት አሃዝ እድገት ዲስኩር ጋር በፍፁም የማይገናኝ መሆኑ ታዉቋል። የዘረኛውና አምባገነኑ ወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በበርካታ መድረኮች በያዝነው የአውሮፓዉያን አመት በኢትዮጵያ የ11.4 በመቶ እድገት እየታየ ነው በማለት ሲመጻደቅና ሲደሰኩር እንደነበር በስፋት ይታወቃል።

ብሉምበርግ የተባለው የዜና አውታር አይ ኤም ኤፍ ይፋ ያደረገውን መረጃ አስመልክቶ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ባለስልጣናት አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ሙከራ ያደረገ ቢሆንም ባለስልጣናቱ ሊገኙ ስላልፈቀዱ አስተያየታቸውን መዘገብ አለመቻሉን አክሎ ገልጿል። የብሔራዊ ባንክ ባለስልጣናቱ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑት የሁሉም ነገር የበላይ ከሆነዉ ከዘረኛዉ መለስ ዜናዊ ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ የሚሆናቸዉን መሪ ቃል እስኪያገኙ ድረስ እንደሆነ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

### የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ እንደደርግ ዘመን ኢትዮጵያዊያን በግዳጅ ሰልፍ እንዲወጡ አደረገ፣ ባለስልጣናቱ በሚሊየኖች የሚቆጠር የህዝብ ገንዘብ ከካዝና በማውጣት በዊስኪ ተራጩ

በዘረኝነት ተወልዶ በዘረኝነት ያደገዉ አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ አፍኖና ረግጦ መግዛት የጀመረበትን ሃያኛ የልደት በዓሉን ባለፈው ቅዳሜ ግንቦት20 ቀን አክብሮ ዉሏል። ከዘረኛዉ አምባገነን ከመለስ ዜናዊ ጽ|ቤት በተላለፈ ትዕዛዝ መሠረት በሚሊዮን የሚቆጠር የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወጥቶ በዓሉን እንዲያደምቅ ለማስገደድ ከማዕከል እስከ ቀበሌ ተዘርግቶ የነበረው መዋቅር ምንም ፍሬ ሳያፈራ ቀርቶ መስቀል አደባባይ የተገኘው ህዝብ ቁጥር ወያኔ በአዲስ አበባ ውስጥ አለኝ ከሚለው የአባላቱ ቁጥር በታች መሆኑን ስልፉን የተከታተለው የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ገለጸ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ወያኔ በትረ ሥልጣን የጨበጠበት የግንቦት 20 ቀን በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ በታሪክ ጠባሳነት የሚታይ ዕለት መሆኑን የሚያዉቀዉ ወያኔ በካድሬዎቹ አማካይነት ህዝቡን ለ”ህዳሴዉ ግድብ” ወጥታችሁ ድግፍ ስጡ በሚል ሰበብ ለመደልል ቢሞክርም አንዳንድ ተገድደዉ ከወጡ ሰዎች ዉጭ መስቀል አደባአበይን የሞሉት የኢህአዴግ አባላት፤ ካድሬዎችና መለስ ዜናዊ ዬኔ የሚላቸዉ ሰዎች ብቻ መሆናቸዉ ታዉቋል። ከዚህ በተጨማሪ የዘንድሮውን በዓለ ንግሥ ለማክበር መንግሥት በሚያስተዳድራቸው መሥሪያ ቤቶችና ተቋሞች ውስጥ ከሚሠሩት የፈረደባቸው የመንግሥት ተቀጣሪዎች በተጨማሪ የግል ትምህርት ቤቶች መምህራንና ሠራተኞች፤ የግል ድርጅት አሰሪዎችና ሠራተኞች፤ ነጋዴዎች፤ ተማሪዎች፤ ወዘተ በሰልፉ ላይ እንዲገኙ ያለውዴታቸው እንዲፈርሙ የደተገደዱ ሲሆን አብዛኛዉ ሠራተኛ ቅዳሜ ጠዋት ወደየሥራ ቦታዉ ሄዶ ሪፖርት ካደረገ ቦኋላ ስሙን አስመዝግቦና ወያኔ ባዘጋጀው የነጻ ትራንስፖርት ተጭኖ ወደመስቀል አደባባይ እንደተወሰደ ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

### ገዢውን ፓርቲ ጥለው የሚጠፉ መኮንኖች ቁጥር እየጨመረ ነው፣ ሁኔታው በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ መንደር ድንጋጤን ፈጥሩአል

ባለፉት ጥቂት አመታት ከገዢው ፓርቲ ጋር የገቡትን “ያለ አቻ ጋብቻ” እያፈረሱ፣ የሚኮበልሉ መኮንኖች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱንና፣ ለኩብለላው የሚሰጡት ምክንያትም በመከላከያ ተቋሞች ውስጥ የሚታየው ዘረኝነት እየጨመረ መምጣቱ ነው ሲል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ምንጮቹን በመጥቀስ ዘገበt።

እንደ ኢሳት ዘገባ ሰሞኑን ከመከላከያ ሰራዊት ራሳቸውን በማግለላቸው እንዲታሰሩ ከተደረጉት መካከል ኮርፖራል ዳንኤል ቶላ፣ ኮርፖራል አሳምነው ግዛቸው፣ ኮርፖራል ሰሎሞን ከላሌ እንዲሁም ኮርፖራል ሰሎሞነ አውግቸው ይገኙበታል። ከዚህ ቀደም ይላቅ መልኬና መስፍን ታደሰ የተባሉ ለሶስትና ሁለት አመታት ታስረው መለቀቃቸው ታውቋል።

ከመከላከያ ሠራዊት በመክዳት አገራቸውን ጥለው ወደ ውጭ አገር ከኮበለሉት መካከል ሌተናት ሀይለ ልኡል ማሞና ካፒቴን ደረጀ ዋቅጅራ የተባሉ መኮንኖች እንደሚገኙበት የዘገበው ኢሳት እነዚህ መኮንኖቹ አሁን ሜታል ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን በሆነው በደጀን አቪየሽን፣ በአየር ሀይልና በኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩና በሙያቸውም አንቱ የተባሉ እንደነበሩ መረጃዎች ያመለክታሉ ብሏል።

የሜታል ኢንጂኔሪንግ ኮሌጅ ዋና ስራ አስኪአጅ የሆነው ጄኔራል ክንፈ ዳኘው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳ ይችላል የሚለው ወሬ በስፋት በሚነገርበት ሰአት መኮንኖቹ ምናልባትም አመጹን ሊመሩ ይችላሉ በሚል ፍርሀት ተይዘው እንዲታሰሩ መመሪያ መስጠቱንም ኢሳት አያይዞ ገልጿል።

በኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ከ96 በመቶ በላይ የሚሆነውን ዋና ዋና የሐላፊነት ቦታዎች የያዙት ከትግራይ ብሄረሰብ የወጡ የህወሃት አባላት በመሆናቸው፣ ከምርጫ 97 ወዲህ መከላከያ ሰራዊቱን እየከዱ የሚጠፉ ወታደሮች ብዙዎች ይስማሙበታል።

### የዘረኛው አገዛዝ ወሰድሁ ያለው የገበያ ዋጋ ማስተካከያ ርምጃ ፤ ገበያውን ይበልጥ እያናጋው መምጣቱን ነዋሪዎች ገለጹ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቀደም ብሎ መሰሪ በሆነው ተንኮሉ ኢትዮጵያዊያንን ከነጋዴው ማህበረሰብ ጋር ለማጋጨት ባደረገው ሙከራ በርካታ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች እውነት መስሉአቸው ከዚህ ቀደም ነጋዴዎችን ሲወቅሱ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን ዋነኛው የችግሩ ምንጭ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ መሆኑን ህብረተሰቡ እየተገነዘበ መምጣቱን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ህዝብን ከፋፍሎ የመግዛት አባዜውን በተለያየ መልኩ ሲተገብር የቆየ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በእቃዎች ዋጋ ላይ የወሰደው ርምጃ በተለይ የአዲስ አበባን ነዋሪዎች ክፉኛ እንዳሰቃየና የከተማዉ ነዋሪ ኑሮ ከምንጊዜም በላይ በከፋ ደረጃ ላይ እንደደረሰ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ገልጿል።

ከዚሁ ክንግዱ ዜና ጋር በተያያዘ አዲስ አበባ ዉስጥ ዘወትር ከቀኑ 6፡00 ጀምሮ ልኳንዳ ቤቶች አዲሱ የዋጋ ተመን በፈጠረዉ ችግር የተነሳ ተዘግተዉ እንደሚዉሉ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ። ኢሳት ከአዲስ አበባ እማኞችን ጠቅሶ ባስተላለፈዉ ዜና መሠረት ነጋዴዎች በወያኔ አገዛዝ ጣልቃ ገብነት የተነሳ ከፍተኛ ኪሳራ ላይ መዉደቃቸዉንና የሠራተኛ ደመወዝ የመክፈል አቅም (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረፋ በየፈርጁ!

የወያኔ ሹማምንት ከተሾሙ ዓመት እንኳን ሳይሞላቸው የናጠጡ ዲታዎች የሚሆኑት በምን ተዓምር ነው? የዚህ ጥያቄ አጭር ምላሽ - በዝርፍያ - የሚል ነው። ዝርፊያው ግን የተለመደው ጨለማን ተገን አድርጎ ነጥቆ መሮጥ አይደለም። የወያኔ ዝርፍያ በቀን ብርሃን "ህግን" ተገን አድርጎ የሚፈፀም ነው። የወያኔ ዋና ዋና የዘረፋ መሠረቶች መሬት፣ የመንግሥት ጨረታ፣ የባንክ ብድር እና እርዳታ ናቸው።

**1. መሬት**

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ "የመሬት ጉዳይ በመቃብሬ ላይ" የሚለው ያለ ምክንያት አይደለም። መሬት ለመለስ ዜናዊ የሚሰጠው አገልግሎት ተዘርዝሮ አያልቅም። በየክልሉ ያሉ ምንዝሮችን ለማባበል አሞሌ ጨው፤ እወህኒ ሊወረውራቸው ሲያሻውም ደግሞ ሰበብ ነው። መሬት ህዝብን ከህዝብ ማጋጨያም ነው። አንዳንዱን በግጦሽ መሬት፤ ሌላውን በክልል፤ ሌላው ደግሞ በዞን ክርክር ገጥሞ ይራኮትለታል። "መሬት አይሸጥም" የሚለው የውሸት ህግ የመሬትን ዋጋ ከአንድ ሺህ ጊዜ በላይ አስወድዶታል። በዛሬዋ ኢትዮጵያ መለስ ዜናዊና ጥቂት የቡድኑ አባላት የዚህ እጅግ ውድ የሆነ የሃገር ሃብት ባለንብረቶች ሆነዋል። ለዚህም ነው መለስ መሬት በመስጠት ብቻ ያሻውን ሰው በአንዲት ቅጽበት ሚሊየነር ማድረግ የሚቻለው።

መለስ እየቸበቸበ ያለው ከላይ ያለውን የገጠር መሬትና የከተማ ቦታን ብቻ ሳይሆን ከርሰ ምድሯንም ጭምር ነው። የመሰቦ ሲሚንቶ ፋብሪካን ማሰሪያ የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ለማግኘት ሲል ለድሃዋ አገራችን የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሊሆን ይችል የነበረውን የወርቅ ማዕድናችንን ለአላሙዲን እጅግ እርካሽ ከሆነ ዋጋ መሸጡም እዚህ ላይ ሊታወስ ይገባል። በዘይትና ሳሙና ችርቻሮ መንግሥት ጣልቃ መግባት አለበት የሚለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የወርቅ ማዕድንን ለግለሰብ ሸጧል። ሺያጩ በተፈፀመበት ወቅት የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 7.14 የአሜሪካ ዶላር የነበረ ሲሆን ዛሬ በ7 ጊዜ በላይ እጥፍ 53.57 የአሜሪካ ዶላር ደርሷል። በዚህ ብቻ አገራችን ያጣችውን የውጭ ምንዛሪ ማሰብ ያስቆጫል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ለም መሬቶችን ለባዕዳን በመስጠት ባለሃገሩን የባዕዳኑ ባርያ የማድረግ ዘመቻ ተጣጡፏል። ዛሬ ለም መሬት ያለው በባዕዳን እጅ ነው። እነሱ የሚያርሱት ለኛ ሳይሆን ለአገራቸውና ለዓለም ገበያ ነው። ግድብ የሚገነባውና መስኖ የሚቆፈረው ለእነሱ ነው።

**2. ጨረታ**

ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ የመንግሥት ጨረታ መብያም፣ ማብያም፤ ማበልፀጊያም ማጥፊያም ነው። ትላልቅ የመንግሥት ጨረታዎች ለውጭ አገር ኩባንያዎች ሲሰጥ በርከት ያለ ኮሚሽን ለወያኔ ባለሥልጣኖች የሚሰጥ መሆኑ ሃሜት ሳይሆን ራሳቸውም በተጣሉ ጊዜ የሚናገሩት ነው። ግድብ፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ ኮንዶሚኒየም፣ ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክ ወይም ሌላ ግንባታ በተሰራ ቁጥር መለስና ጓደኞቹ ኪሳቸውን ያደልባሉ። አጫፋሪዎቻቸው ወደ ሰማይ ይመነጠቃሉ። በዛሬ ጊዜ በጨረታ መስጠት ሥራ ያሉ የመንግሥት ባለሥልጣናትን እና የጨረታ ሥራ የማግኘት እድሉ ያላቸው ተቋራጮችን ብንመረመር በመለስ ዜናዊ ቤተሰቦች የተሞሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። የህዳሴ ግድብ ለተባለው የውሸት ፕሮጀክት ሲሚንቶ አቅራቢው ያው የመለስ ቤተሰብ ኩባንያ መሆኑ እየተነገረ ነው።

**3. የባንክ ብድር**

ስለባንክ ብድር ተደጋግሞ የተነገረ ጉዳይ ነው። የዋጋ ንረቱ 70 እና 80 በመቶ ሆኖ እያለ እነሱ በ 10 በመቶ ወለድ ከባንክ እየተበደሩ ህንፃ ሲገነቡ ማየት እጅግ የሚሰቀጥጥ ነው። እነሱ በመበደራቸው ህዝቡ ጾሙን እያደረ 60 እና 70 በመቶ ጭማሪ ይሰጣቸዋል ማለት ነው። ለግል ጥቅም ሲባል የዋጋ ንረትን አውቆ መፍጠር በሰብዓዊነት ላይ የሚደረግ ወንጀል ነው።

አሁን ደግሞ ይኸው የዘረፋ ብድር ስሙን ቀይሮ "ቦንድ" ተብሎ መጥቷል። በ70 በመቶ የዋጋ ንረት ለቦንድ የ 5 በመቶ ወለድ መክፈል 65 በመቶውን መብላት ማለት ነው።

**4. እርዳታ**

ገና ከጠዋቱ ወያኔን በእግሩ ያቆመው ለድሃው የመጣው እርዳታ ነው። መስከረም 1978 ዓም የህዋህት ፓሊት ቢሮ በድርቅ ለተጎዳ ሕዝብ የመጣውን እርዳታ 55 በመቶው ለማሌሊት ማጠናከሪያ፤ 40 በመቶው ለቀይ ሠራዊት፤ እና 5 በመቶው ደግሞ ለሕዝብ ይከፋፈል ሲል ወሰነ። በዚሁ አመዳደብ ለሕዝብ ብለው ያስቀመጡት 5% ቢሆን ለማንም አልተሰጠም። ይህንን በስብሰባው የነበሩ አባላት ለዓለም ነግረዋል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለምግብ፣ ለመጠጥ ውሃ፣ ለመድሃኒት እና ለትምህርት እየተባለ እርዳታ ወደ ኢትዮጵያ ይፈሳል። የፀረ-ሽብርተኝነት ትግልም ሌላ ራሱን የቻለ የእርዳታ ቧንቧ ሆኗል። በእርዳታው ቧንቧ አፍ ላይ የተደቀነው ግን ወያኔ ነው።

ገበናቸውን ሲሸፍን የቆየው የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) የወያኔ አገዛዝ ከ1990 እአአ ወዲህ በነበሩት 18 ዓመታት ውስጥ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማለትም 150 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ከሃገር ማሸሹን መስከሯል። ገንዘብ የማሸሹም ተግባር ከ1997 ምርጫ በኋላ እየተባባሰ መምጣቱ የዩ.ኤን.ዲ.ፒ ጥናት አረጋግጧል።

ለእርዳታ እህል እጁ ያልተሰበሰበ እንደምን መዋጮ ሰብስቦ ግድብ ያሰራል ተብሎ ይታመናል?

የወያኔ ዘረፋ "የህግ" ሽፋን ያለው በመሆኑ በቀላሉ ላይታይ ይችላል። "መሬት አይሸጥም" ሲል ለድሃው ያሰበ ይመስል ይሆናል። እሱ ግን ይሸጣል። መንገድና ድልድይ፤ ግድብና መስኖ የመሳሰሉ ግንባታዎችም ሹማምንቱ ለሚያገኙት ጉርሻ ሲሉ የሚሯሯጡላቸው ነገሮች ናቸው። የባንክ ብድርም ስውር መዝረፊያቸው ነው። እርዳታ የተለመደ መክበሪያቸው ነው።

ይህ እኩይ ኃይል ለማንኛውም ዘለቄታዊና አገራዊ የልማት ሥራ የሚታመን አይደለም። መለስና በዙሪያው የሰበሰባቸው ሰዎች የሚሊኒየሙ ዘራፊዎች መባል ይኖርባቸዋል።

**ዘረፋ ሰለቸኝ፤ አንገፈገፈን፤ በቃን፣ በቃ!!!!**

### የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አመጹ፣ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የጽህፈት መሳሪያዎቻቸዉንና የመማሪያ መጽሐፍቶቻቸዉን እንደያዙ በሠላማዊ መንገድ ፍትሃዊ ጥያቄዎችን ላነሱ ተማሪዎች የሃገሪቱ ፌደራል ፖሊስ እንደዚህ አይነት ፍትህ የጎደለዉና የጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ሲወስድ የመጀመሪያ ግዜ አለመሆኑን የገለጸዉ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ወያኔ በህዝብ ትግል በአጭር ግዜ ዉስጥ ከስልጣን ካልተወገደ ተቃዉሞ በገጠመዉ ቁጥር ህዝብን ከመግደልና ከማሰቃየት ወደ ኋላ እንደማይል ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንዳንድ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ገልጸዋል።

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ተቃዉሟቸዉን በገለጹበት ወቅት ለሆዳቸዉ ያደሩ በአርባ ምንጭና በአካባቢዋ የሚገኙ የዘረኛው ስርዐት ሹመኞችና አጨብጫቢዎች ከፌደራል ፖሊስ ጋር በማበር ተማሪዎችን መደብደባቸውን አስተያየታቸዉን የሰጡ ተማሪዎች ገልጸዋል። በዚህ ጭካኔ በተሞላበት የድብደባ እርምጃ በአካባቢዉ የሚገኙ የወያኔ ካድሬዎች በከፍተኛ ደረጃ መሳተፋቸዉን ከስፍራዉ በደረሰን ዜና ለማወቅ ተችሏል።

በአርባ ምንጭ ከተማ የሚገኙ የአይን እማኞች ለዘጋቢያችን በሰጡት አስተያየት ደግሞ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔአገዛዝ "የዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች ንብረታችሁ የሆነውን ዩኒቨርሲቲ እያወደሙት ነው፣ እንዴት ዝም ብላችሁ ትመለከታላችሁ" በማለት ሆን ብሎ የአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪዎችን ለማነሳሳት እና ከተማሪዎቹ ጋር በማጋጨት እርስ በርስ ለማፋጀት ሲቀሰቅስ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

### መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ የዘረፉት 8.4 ቢሊዮን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የጠበቁ ለያንዳንዱ ክልል አሥር የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በድምሩ 90 ፤ ለእያንዳንዱ ክልል በነፍሰወከፍ 2 ሁለት ዩኒቨርሲቲዎችን በድምሩ 18፤ ለያንዳንዱ ክልል ሶስት ኮሌጆች በድምሩ 27፤ ለያንዳንዱ ክልል 4 ዘመናዊ ሆሲታሎች በድምሩ 36 ፤ ለያንዳዱ ክልል ሃያ ጤና ጣቢያዎች በድምሩ 180፤ ለ 3 ክልሎች ሁለት ሁለት የዘይት ፋብሪካዎች በድምሩ 6፤ አገሪቷ ውስጥ ከፍተኛ እጥረት እንዳለ የሚወራለትን 4 የስሚንቶ ፋብሪካዎችን እንዲሁም አራት እጂግ ከፍተኛ የሚባሉ አግሮ ኢንደስትሪዎችን በመገንባት የአገሪቷን ችግር ሊቀርፍ የሚችል እንደሆነ በስፋት ገልጸዋል።

በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ዉስጥ ከአርባ በመቶ በላይ የሚሆነው ዜጋ የቀን ገቢው ከአንድ የአሜሪካን ዶላር በታች ሲሆን ከአራት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን የሚኖሩት በአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ርዳታ ነዉ ፣ ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የአገሪቱ ዜጋ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሆዱን እንኳን ሞልቶ ማደር ያልቻለ ህብረተሰብ እንደሆነ በስፋት ይታወቃል።

### የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት አሁን ካለበት 7.5 በመቶ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኢትዮጵያ ዉስጥ የዋጋ ግሽበት ወደ ሰላሳ በመቶ የማሻቀቡን ጉደይ የዘረኛው ስርዐት መሪዎች እራሳቸዉ አምነዉ የተቀበሉት ቢሆንም በርካታ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች በሃገር ውስጥ ያለው ነባራዊ ሁኔታና የሸቀጦችን ዋጋ መናር ከግምት ውስጥ ሲገባ የዋጋ ግሽበቱ የዘረኛው አገዛዝ በይፋ ካመነው፣ ሁለትና ሶስት እጥፍ በላይ ሊሆን እንደሚችል አጥብቀው ይከራከራሉ።

የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ለማስተካከል በሚል የዋጋ ተመን አውጥቶ የነበረ ቢሆንም፣ የወጣው ተመን ምንም ውጤታማ ካለመሆኑም በላይ ሃገሪቱን ወደባሰ የኢኮኖሚ ቀውስ እንድትገባ ማድረጉ በስፋት ሲዘገብ የቆየ መሆኑ ይታወሳል።

ከዚሁ ዜና ጋር በተያያዘ አገዛዙ በሸቀጦች ዋጋ ላይ ያወጣው ተመን ተግባራዊ መሆን ሳይችል በመቅረቱ የሸቀጦች ዋጋ ቀድሞ ወደነበረበት እየተመለሰ ሲሆን ከትናንት በስቲያ ጀምሮ የአንድ ኪሎ ስጋ ዋጋ ከዘጠና ብር በላይ እንዲሆን መደረጉን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገልጿል። የስጋ ዋጋን እንደገና ወደነበረበት የመመለስ ጉደይ አስመልክቶ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የስጋ ቤት ባለቤቶች በሰጡት አስተያየት ድሮውንም ቢሆን የተወሰደው ርምጃ በፍጹም ተግባራዊ ሊሆን የማይችል፣ ነጋዴውን ከሸማቹ ጋር በማጋጨት የትኩረት አቅጣጫን ለማስቀየስ ታልሞ የነበረና ምንም ፋይዳ የሌለው ነበር፣ አሁንም ቢሆን ይህ የስጋ መሸጫ ዋጋ ሙሉ በሙሉ ሊያዋጣ የማይችል በመሆኑ የስጋ ዋጋ አሁን ከሚታየዉ በላይ በእጥፍ ሊያሻቅብ እንደሚችል ግምታቸውን ሰጥተዋል።

### የዘረኛው አገዛዝ ወሰድሁ ያለው የገበያ ዋጋ ማስተካከያ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እስከማጣት መድረሳቸውን አሳዉቀዋል። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ችግሩን ካልተስተካከለ ሙሉ ለሙሉ ከገበያ እንደሚወጡ ማስጠንቀቃቸው ታውቋል። ነጋዴዎቹ ይህን አቋማቸውን ያስታወቁት፤ ሰሞኑን በማህበራቸው አማካይነት ለንግድ ሚኒስቴር በፃፉት ደብዳቤ ላይ መሆኑን ኢሳት አያይዞ ዘግቧል።

በንግዱ ህብረተሰብ አካባቢ የተከሰተዉ ችግር ወደ ግብርናዉ መስክ ዘልቆ በመግባት ገበሬው የቁም ከብት ማድለቡን ጨርሶ እንዲተው ከማድረጉም ባሻገር ቀደም ሲል ለቁርጥ የሚሆን ስጋ ያቀርቡ የነበሩ ነጋዴዎች የበግና የፍየል ስጋ እየጠበሱ ወደ ለመሸጥ ተገድደዋል። ይህ ደግሞ የፍየልና የበግ አቅርቦትና ፍላጎትን በማዛባት የበግና የፍየል ዋጋ ከሸማቹ ህብረተሰብ የመግዛት አቅም በላይ በከፍተኛ ፍጥነት እንድያድግ ማድረጉን ኢሳት በዘገባው ላይ አመልክቷል።

የዘረኛውና የአምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የዋጋ ንረትን ለማስተካከል በሚል የሚወስዳቸው እርምጃዎች የአገሪቱን ኢኮኖሚ ከቀን ወደቀን እጅግ በጣም ወደ ከፋ ቀውስ ዉስጥ በመከተታቸዉ የአገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ የሶማሊያና የሲያድ ባሪ እጣ ፋንታ ይገጥመናል ብሎ ለነጋዴውና ለባለስልጣኖቹ እስከመናገር መድረሱ ይታወቃል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# የህዝባዊ እምቢተኛነት የነጻነት ትግል በፖለቲካ ድርጅቶች የመመካከርና የመተባበር አጀንዳ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ

(ለግንቦት 7 አባላት ለውይይት የቀረበ ጽሁፍ፤ ግንቦት 2003) (ክፍል 1 )

**1. የወቅቱ የትብብር ጥሪ ልዩ ገጽታዎች**

የሃገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች "እንሰባሰብ፣ እንቀናጅ፣ ትብብር እንፍጠር" በማለት መድከማቸውን እናውቃለን። እስካሁን የድካማቸው ውጤት ግን ፍሬ አፍርቶ አልታየም። ትብብሩ ያልተሳካበት ምክንያት ብዙ ነው። እያንዳንዱ ድርጅትም ያልተሳካበትን ምክንያት በራሱ መነጽር እንደሚያየው ይታወቃል። እነዚህን ምክንያቶች መዘርዘር የዚህ ጸሁፍ አላማ አይደለም። አሁንም ቢሆን ይህ የመተባበር ጥያቄ አንገብጋቢ ነው። ዛሬ ተገንብቶ ነገ የሚፈርስ ሳይሆን በከፍተኛ የህዝብ ወገንተኛነት፣ የሃገር ተቆርቋሪነት ላይ የተመሰረተ በድርጅቶች መካከል የሚታዩ ችግሮችን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰባችንን የተወሳሰቡ ችግሮች ለመፍታት አልሞ የተነሳ ስትራቴጂያዊ ግብ ያለው የሁሉም ድርጅቶች ትብብር እንደሚያስፈልገን አጠያያቂ አይደለም። በዚህም ምክንያት የግንቦት 7 ንቅናቄ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ትብብር ለመፍጠር የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ ይቀጥላል።

የዚህ ጽሁፍ አላማ ከላይ የተጠቀሰውንና ብዙ ስራ የሚጠይቀውን፤ የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱ፣ ነጻነቱ፣ አንድነቱ እንዲከበር ሰላሙ እንዲረጋገጥ፤ በርጋታ ፊቱን ወደ ልማት አዞሮ የሰውና የተፈጥሮ ሃብቱን በሚገባ በመጠቀም አዋራጅ ከሆነው ድህነት እንዲላቀቅ አስፈላጊ የሆነው የሃገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር አስፈላጊነት ወደ ጎን ያደረገ አይደለም። ይህ ጽሁፍ ያተኮረው ከዚህ ቀደም ስለትብብር ስንመካከር በአካባቢያችን ያልነበረው የቱኒዝያና የግብጽ ህዝባዊ እምቢተኛነት አዲስ ታሪካዊ ክስተት በፖለቲካ ድርጅቶች የመተባበር ጥያቄ ላይ ይዟቸው የመጣቸውን ያልተጠበቁ ጫናዎች ለመፈተሽ ነው።

ከሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ ህዝባዊ አብዮቶች በኋላ እየተነሳ ያለው የእንነጋገር፣ የእንመካከር እና የእንተባበር ጥያቄ ካለፉት የመተባበር ጥያቄዎች የተለየ ነው። የአሁኑ ጥያቄ መነሻው የድርጅት መሪዎችና የአባላቶቻቸው ፍላጎት አይደለም። ይህን ማለት ግን ድርጅቶችና አባላቶቻቸው በሰሜን አፍሪካ ህዝብ ታሪክ ሰሪነት አልተነኩም ለማለት አይደለም። የወቅቱ የትብብር አስፈላጊነት ጥሪ በቱኒዝያና በግብጽ የታየው ህዝባዊ እምቢተኛነት በመላው ህብረተሰባችን በተለይ ከፖለቲካ ልሂቁ ወጭ ባለው ህብረተሰብ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ነው።

የሰሜን አፍሪቃው ህዝባዊ እምቢተኛነት የተቃዋሚ ድርጅቶችን መሪነት አልፈለገም። በተመሳሳይም የድርጅቶችን መሪነት የማይጠብቅ ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ ይነሳል የሚል ግምት አለ። ስለዚህም የአሁኑ "እንጋገር፣ እንመካከር" አይቀርም ተብሎ የሚጠበቀውን የሃገራችን ህዝባዊ ቁጣ እሳቤው ያደረገ ነው።

የሚከተሉት ጥያቄዎች እየተነሱ ነው።

- የቱኒዚያና የግብጽ አይነቱ ህዝባዊ አመጽ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲነሳ ምን ማድረግ ይገባናል?
- ህዝቡ ለራሱና ለተቃዋሚ ድርጅቶች በነጻ የመንቀሳቀስ መብት የሞት የሽረት ትግል ወደሚያደርግበት ሁኔታ እየገባ ነው። በዚህ ወቅት ህዝብን ነጻ እናወጣለን ብለው የተደራጁ ሃይሎች ነጻ ሊያወጣቸው የተነሳውን ህዝብ ዝም ብለው ሊያዩት ነወይ?
- በግብጽና በቱኒዝያ ህዝባዊ አብዮት ምክንያት ታግደው የነበሩ፤ ተሰደው የነበሩ፤ ተቀብረው የነበሩ ድርጅቶችን ነጻ አውጥቷል። በኛስ ሃገር ይህ የማይሆንበት ምክንያት ይኖራልን?
- ከዚህ ቀደም በጋራ እንስራ እንተባበር የሚሉ ጥረቶቻችን አልተሳኩምና አሁንም ምንም ነገር ማድረግ አንችልም ብለን እንቀመጥ ወይ?
- ህዝብን እኛ ተቃዋሚዎች ልዩነቶቻችንን አስወግደን ትብብር አልፈጠርንምና መነሳትንህን አቁም እንበለው? ብንለውስ እሺ ብሎ ያቆማል ወይ? ይህስ አቋም በታሪክ የሚያስጠይቅ አይሆንም ወይ?

ከላይ ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች በሚሰጧቸው መልሶች አብዛናኛዎቹ ድርጅቶች ይስማማሉ ብለን እናስባለን።

የምክክር አስፈላጊነትና አጣዳፊነት በሁሉም ጸረ- አምባገነናዊነት ሃይሎች ተቀባይነት ይኖረዋል ብለን እንድናምን ያደረጉን ተጨማሪ እሳቤዎች አሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ስለቱኒዝያና የግብጽ ወጣትና ማህበረሰብ ክንውኖች የሚያሳየውን አድናቆትና አክብሮት ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት የቆሙ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪል ማህበራት ሁሉ ይጋራሉ። እነዚህ ሃይሎች በግብጽና በቱኒዝያ የታየው ተመሳሳይ ሁኔታ በሃገራችን ቢፈጠር እጅግ ይደሰታሉ። ተቃዋሚዎች እራሳቸው ተሰባስበውና ተጠናክረው ማምጣት ያልቻሉትን ለውጥ ህዝብ ባጭር ጊዜ ማምጣት መቻሉ እርካታ የሚሰጣቸው ይሆናል። ባለንበት ወቅት "እኔ ካልመራሁት ህዝብ መነሳት የለበትም፤ እኔ ያልመራሁት ለውጥ መምጣት አይገባውም" ብለው የሚያስቡ ድርጅቶች አይኖሩም። "ህዝብ ቢያምጽና አመጹም ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ምስረታ እስከሆነ ድረስ ሁሉም ድርጅቶች አመጹ ለማቀጣጠል የሚባትለውን ህዝብ እንዴት እናበረታተው? እንዴት እንደግፈው?" በሚል ጉዳይ ላይ ለመመካከር ጥሪ ብናደርግ ተቃውሞ አይኖራቸውም የሚሉት እሳቤዎች ግንቦት 7 ንቅናቄን ለምክክሩ ተግቶ እንዲሰራ አድርገውታል።

በእነዚህ እሳቤዎችት ትክክለኛነት ላይ ተማምነን የግንቦት7ና የጥምረት ለፍትህ ለነጻነትና ለእኩልነት አባል ድርጅቶች አመራር አካላት ከሁሉም የነጻነት ግንባሮች፣ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት ጋር ለመመካከር ሞክረናል። በኛ በኩል የቱኒዝያና የግብጽ አብዮቶች የከፈቱልን የጸረ-አምባገነንነት የትግል አግባብ እርስ በርሳችን ለመነጋገሪያ የሚሆን አጣዳፊና ተጨባጭ የምክክር አጀንዳ ይዞልን መጥቷል የሚል እምነት አለን። በመሆኑም ድርጅቶችን በተናጠልም ይሁን በጋራ፤ ትንሽ ትልቅ ሳንል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊቀሰቀስ ስለሚችለው የህዝባዊ እምቢተናኛነት አመጽና የተቃዋሚ ድርጅቶች ሚና ጉዳይ ላይ ለማማካር ጥረት አድርገናል። ይህን ጥረታችንን እንድንቀጥልበትና ብሎም ወደላቀ የምክክርና የትብብር ደረጃ እንዲሚያድግ ተስፋ እንድንሰንቅ የሚያደረግ አበረታታች ሁኔታዎች እያየንበት ነው። ይህ ጽሁፍ በአዲሱ የትብብር ምንነት ዙሪያ አሉ ብለን የምናስባቸውን ውዥንብሮችና ሌሎችንም የመተባባር ጥረታችን ደንቃራ የሆኑ ጉዳዮችን የምናጠራበት ነው።

**2. ትንሽ እገዛ ብቻ የሚሻ ህዝብና የምክክር አስፈላጊነት**

የሃገራችን ህዝብ በግብጽና በቱኒዝያ ወንድምና እህቶቹ ክንውኖች ተነቃቅቷል። ከዚህ በተጨማሪ በሚፈጸምበት ግፍና የቀን ከቀን ህይወቱን ሲኦል ባደረገበት አዋራጅ ድህነት ተማሯል። ይህ ህዝብ እንደ ሰሜን አፍሪካ ህዝቦች የራሱን የፖለቲካ እጣ በጁ ለማድረግ እየተቁነጠነጠ ነው። ነገር ግን ይህ ጥረት በኢትዮጵያ ዉስጥ በሚገኙ ልዩ ሁኔታዎች የተነሳ እንደሌሎች ሃገሮች ቀላል ላይሆን ይችላል። ወያኔ ህብረተሰቡን በዘርና በሃይማኖት እንዲሰነጣጠር እርስ በርሱ እንዲጠራጠር አድርጎታል። የግብጽና የቱኒዚያ ወጣትና ዜጋ እርስ በርሱ ለመነጋገርና መረጃ ለመቀያየርና በጋራ ለማቀድ የተጠቀመባቸው ዘመናዊ በተለይ ከኢንተረኔት ጋር የተያያዙ የኮምኒኬሽን ቴክኖሎጂ ግብአቶች በሃገራችን አልተስፋፉም። ያለውንም ቢሆን የሚጠቀመው ቁጥር አነስተኛ ነው። የመጠቀም እውቀቱም ደካማ ነው። በከተሞች ኗሪ የሆነው ህዝብ አነስተኛነትነው። ከተሞችን ማእከል ያደረገውን የአረብ ሃገሮች ህዝባዊ አመጽ በኢትዮጵያ ለመድገም ይህ ጭብጥ በራሱ ፈተና ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የሃገራችን የጦር ሃይል እንደ ሰሜን አፍሪካ ሃገሮች ሃገራዊና ህዝባዊ ተፈጥሮ የለወም። ከዚህም የተነሳ ህዝብ ለነጻነቱና ለመብቱ መከበር ቢነሳ ይህ ጦር እንደግብጽና እንደ ቱኒዝያ ጦር ከህዝብ ጋር ይቆማል ወይንስ ከመለስ ዜናው ጋር ልሙት ይላል? ገና ተጨባች መልስ ያልተገኘለት ጥያቄ ነው። እንደነ ቱኒዝያ ለተወሰነ ጊዜ ችግር መቋቋም የሚችል መሃከለኛ ገቢ ያላቸው በርካታ ዜጎች በሃገራችን የሉም። የሃገራችንን የመገናኛ ብዙሃንም ስርጭት፣ የቴሌቪዥን፣ የሬድዮ የጋዜጣዎች መስፋፋት ህዝባዊ እምቢተኛነቱን በሚያስገርም ክህሎት ካካሄዱት ሃገሮች ጋር ካነጻጸርነው እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። የውጭ ሚድያ ትኩረት፣ ሚድያዎቹ የሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎችና ለኢትዮጵያም ሊሰጡ የሚችሉት የሽፋን ጊዜ አነስተኛነት በህዝባዊ እምቢተኛነቱ ስሉጥነት ላይ የራሳቸውን አሉታዊ ጫናዎች ያሳድራሉ።

ኢትዮጵያን ከነግብጽና ከሌሎች ሃገሮች የሚለይዋት ጭብጦች የሃገራችን ወጣትና ህዝብ በራሱ ሃይል ተንቀሳቅሶ የልቡን እንዳያደርስ ደንቃራዎች እንደሚሆኑበት ግልጽ ነው። እነዚህ ደንቃራዎች በሙሉ ባይጠረጉም የሃገራችን ህዝብ በታሪኩ ከግፍና ከጭቆና ጋር ካደረገው የትግል ታሪኩ ከሚያገኘው የመንፈስ ጥንካሬና የመስዋእትነት ዝግጁነት ተበረታትቶ አሻፈረኝ ብሎ መነሳቱ አይቀርም። ፈተናዎቹ ከባድና ብዙ ስለሆኑ የሃገራችን ህዝብ፣ በተለይ ወጣቱ በዚህ ወሳኝ ወቅት የሚደረግለትን ማንኛውን ድጋፍ በሙሉ ለመቀበል ዝግጁ ነው። በዚህ ፈታኝ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ እገዛ ይፈልጋል። ከሃገር ውስጥ የሚመጡ የወጣቱ ጥያቄዎች ስንመለከት ወጣቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዲያደረጉ የሚጠይቋቸው

*ሁላችሁም ህዝባዊ እምቢተኛነት አመጽ እንዲቀጣጠል እንደምትፈልጉ እናውቃለን። የእኛም የናንተም ፍላጎት አንድ መሆኑን ተረድተናል። እውነተኛ ፍላጎታችሁ ይህ ከሆነ እባካችሁ ዝብርቅርቁ የወጣ፣ እርስ በርሱ የሚጣረስ፣ ትርጉምና መልእክቱ ለወጣቱም ሆነ ለህዝቡ የማይገባና ውዥንብር የሚያስፋፋ ወረቀት በህብረተሰባችን ውስጥ አትበትኑ። በጋራ መክራችሁ የህዝባዊ እምቢተኛነቱ ትግል የሚያተኩሩባቸውን ጥያቄዎች አሳውቁን።*

የሚሉ ግልጽና ቀላል ነገሮችን ነው። የተበተኑትን የሚገርሙ ወረቀቶችን ፎቶ እያነሱ ለንቅናቄያችን በኢሜል ልከዋል። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት እኛ ተባብረን ባንድ ቃል ካልተናገረን ወያኔ በእያንዳንዳችን ስም የፈለገውን ወረቀት እያባዛ ቢበትን የሚከለክለው አይኖርም። አንዳንዶቹ በራሪ ወረቀቶች የሚያነሱትን ህዝብ ከህዝብ የሚያጋጭና ህዝብን የሚያስበረግግ ጽሁፍ ለተመለከተ የወያኔ እጅ እንዳለበት ግልጽ ነው።

በግንቦት7 በኩል የምናነበው ሃገራዊ ሁኔታ የሚጠቁመው ህዝብ የዘር፣ የሃይማኖትና ሌሎችንም ከፋፋይ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ወደ ጎን አድርጎ ሁሉንም እያዋረደ ባለው የወያኔ አገዛዝ ላይ የድርጅቶችን መሪነት ሳይጠብቅ ለመነሳት እያኮበኮበ መሆኑን ነው። የሃገራችን ወጣቶች "ድርጅቶች መሩን አልመሩን በራሳችን ተደራጅተን ለነጻነታችን የሚከፈለውን መስዋእትነት ከፍለን ነጻ ልንወጣ ቆርጠናል" የሚል መግለጫ እያወጡ ነው። የኦሮሞ ብሄራዊ ወጣቶች እንቅስቃሴ ያወጣው መግለጫ ወጣቱ የየትኛውንም ድርጅት ቡራኬ እንደማይጠብቅ ገልፆ አድርጓል። ትክክል፣ወጣቶቹ ፍትሃዊና የሃገሪቱን ወጣትና ህዝብ በጋራ በወያኔ ላይ ሊያስነሱ ይችላሉ ያላቸውን ጥያቄዎችን ዘርዝሮ አስቀምጠዋል። የኢትዮጵያ ወጣቶች ንቅናቄ የተባለው ሌላው የወጣቶች ቡድን "የኦሮሞ ወጣቶች ያቀረቧቸው ጥያቄዎች የኔም ናቸው" በማለት ድጋፉን ሰጥቷል። ሌሎችም ወጣቱን በበስፋት የሚያሳትፉ ዘመናዊ የማህበራዊ የመረጃ ድሮች ይህንን የወጣቶቹን ጥያቄ እያስተጋቡ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ወጣቱ በብዛት በሚገኝባቸው ቦታዎች ወጣቱን ለለውጥ እንዲነሳ የሚጠሩ ወረቀቶች ይበተናሉ። የፖለቲካ ድርጅቶች አገዝነውም አላገዝነውም ወጣቱ ለለውጥ መነሳቱ አይቀርም።

በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ የፖለቲካ ድርጅቶች ምን ያድርጉ? ይህ የወጣቶች ሙከራ እንዲሳካ የድርሻችን ልንወጣ የግድ አይደለም ወይ? ጥያቄው የፖለቲካ ድርጅቶች ከነግዙፍ ድክመቶቻቸን ይህን የወጣትና የህዝብ መነሳሳት የሚያግዙ ስራዎች መስራት አንችልም ወይ? የዘመኑ ፍቱን የስርአት መቀየሪያ መሳሪያ የሆነውን ህዝባዊ እምቢተኛነትን የመጠቀም ታሪካዊ እድል የሃገራችን ህዝብ እንዳያልፈው የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራና በፍጥነት ተመካክረው አንድ ነገር ማድረግ አይኖርባቸውም ወይ? እነዚህ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ የሚጠይቁ መሆናቸው ነው፣ በድርጅቶች መሃል የመመካከርና የመተባበርን ጉዳይ አስቸኳይ ያደረገው።

(ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

### ግንቦት 7 ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ላይ የወጣበትን 20ኛ የድል በዓል የሚያከብርበትን ዕለት አስመልክቶ መግለጫ አወጣ

ወያኔ ደርግን ከስልጣን ያባረረበትንና በትረ ሥልጣን በእጁ ያስገባበትን 20ኛ አመት የሚያከብርበት የዛሬዋ ዕለት ለኛ ለኢትዮጵያዊያ ሃያ የመከራ፤ የስቆቃና የባርነት አመታት እንደነበሩ በማስታወስ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከትናንት በስቲያ ግንቦት 18 ቀን 2003 አም መግለጫ አውጥቶአል።

ያለፉት ሃያ የወያኔ የሥልጣን አመታት ፤ ለመጀመሪያ ግዜ በሃገራችን ታሪክ ከአንድ ዘር ብቻ የተሰባሰቡ ጥቂት ግለሰቦች የሃገሪቱን ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ስልጣን፤ የሃገሪቱን ሃብት፣ መሬቱንና ማዕድኑ፤ የሃገር ውስጥና የወጭ ሃገር ንግዱን፤ የኮንስትራክሽን፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ፣ የትራንስፖርት፣ የማምረቻና ማከፋፈያ ስራውን የተቆጣጠሩበት፤ እፍረትና ይሉኝት የለሽ ነውረኛና አደገኛ ስራ የተሰራባቸው አመታት ናቸው ያለው ግንቦት 7 ፤ ዛሬም እንደ ትናንቱ ህዝብ የሃገሩንና የራሱን አራጆቹ ድግስ እንዲያሞቅና ለዲስኩራቸው እንዲያጨበጨብ እየተደረገ ነው በማለት "ወያኔ ወጥታችሁ የንግስና በአሌን በድምቀት አክብሩልኝ" በማለት ህዝብ ሲያስገድድ መሰንበቱን አውግዞታል።

መግለጫው በመቀጠልም ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የነበሩት 20 አመታት በየትኛውም ዘመን ስልጣን ላይ የወጡ ገዥዎች አስበውትና አድርገውት በማያውቁት ደረጃ የሃገር ሃብትና ቅርስ ስልጣን ላይ ባሉ ጥቂት የትግራይ ገዥ ጉጅሌ አባላት እየተዘረፈ በባእድ ሃገራት የተከማቸ እንደሆነ ገልጾ ፤ የዘረኛው ገዥ ጉጅሌ አባላት ለዘረፋ እንዲያመቻቸው ያስጠጓቸው የውጭ ሃገራት ዜጎች በሃገራችን ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የህዝቡን ለም መሬት፣ ወርቅና ሌላም ማእድን እንዳሻቸው እየዘረፉና የሃገሪቱን ህዝብ ከባርነት ስርአት ባለተናነሰ የጌታና የሎሌ ግንኙነት እንዳሻቸው እያዋረዱ እንዲያሰሩ ስድ የተለቀቁባቸው አመታት መሆናቸውን አስምሮበታል።

### በኢትዮጵያ የሙስና መስፋፋት ከቁጥጥር ውጪ መውጣቱ ተገለፀ

ባለፉት 10 ወራት ዉስጥ ወያኔ በተለያየ ግዜ የሾማቸዉንና ታማኝነታቸውን እጠራጠራለሁ ያላቸዉን ተሿሚዎቹን በውንጀላ ለማባረር ባቋቋመው የፀረ ሙስና ፍርድ ቤት ከተከሰሱት በርካታ አባላቶቹ መካከል 186ቱ ጥፋተኛ ሆነዉ መገኘታቸዉን ኮሚሽኑ ለፓርላማዉ የህግ፤ የፍትህና የአስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበዉ ሪፖርት መግለጹን ለማወቅ ተችሎአል።

ነዉ ቢዝነስ ኢትዮጵያ የተባለው የመረጃ ምንጭ እንደገለፀዉ ኮሚሽኑ ክስ ከመሰረተባቸዉ መካከል 50 የሚሆኑት ያላግባብ የተከሰሱ ናቸው በማለት ፍርድ ቤት ክሱን ዉድቅ አድርጎታል። በወያኔ ቁንጮዎች የሚፈጸመውን ሙስናና ዘረፋ የማየት መብት የተነፈገው የሙስና ኮሚሽኑ ሙስና በስፋት ይካሄድባቸዋል የሚባሉትን መንግሥታዊ ተቋሞች አስመልክቶ መመሪያ ለማዘጋጀት እንዲረዳዉ 42 በሚሆኑ የስራ ሂደቶች ላይ ጥናት በማድረግ ላይ እንደሆነ ገልጾ ከነዚህም የ26ቱ ጥናት ተጠናቅቆ ይፋ ሆኗል። በዘገባው መሠረት የጨረታ አፈፃፀም፤ የሰራተኛ ቅጥር፤ የእቃ ግዢና ሽያጭ፤ የንብረት ማስተላለፍና፤ የፕሮጀክት ፋይናንስ አያያዝን የመሳሰሉት ለሙስና ቀዳዳ የሚፈጥሩ የስራ ሂደቶች እንደሆኑ በሪፖርቱ ተገልጿል።

ለሙስና ከተጋለጡት መካከል፡ የአዶላ የወርቅ ማእድን ኢንተርፕራይዝ፣ የኢትዮጵያ የሸቀጣ ሸቀጥ ልወዉጥ/ ኮሞዲቲ ኤክስቼንጅ፣ የኢትዮጵያ የጉምሩክና የገቢ ቀረጥ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽንና የኮሙኒኬሽን አጀንሲ፣ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን፣ የዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የገጠር የኤሌክትሪክ ፈንድ እና የዉሃ ሃብት ሚኒስቴር፣ ማእከላዊ ስታትስቲክስ፣ ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ፣ የሲቪል አቪየሽን ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ የአዉሮፕላን ማረፊያዎች ኢንተርፕራይዝ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የኮንስራክሽን ዲዛይን፣ የመቀሌና የአዋሳ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የዘዉዲቱና የቅዱስ ፓዉሎስ ሆስፒታሎች፣ የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አራዳና ቂርቆስ ክፍለ ከተማዎች፣ የድሬዳዋ የመንገድ ትራንስፖርት መ/ቤት ይገኙባቸዋል ተብሏል።

ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ ባለፈው ዓመት አላግባብ ለግለሰቦች የተሰጠ 14800 ሰኩዌር ሜትር መሬትና 2 ቢሊዮን ብር ማስመለሱን ገልጿል። በሌላ በኩል ደግሞ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ወደግል ንብረትነት በተዛወረበት ወቅት አላግባብ ለመንግስት ገቢ ሳይሆን የቀረ 3.5 ሚሊዮን ብር ጥሬ ገንዘብና 3.8 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ንብረትና እንዲመለስ ማድረጉን ኮሚሽኑ አያይዞ ገልጿል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ፀረ ሙስና ኮሚሽን ተብየው በወያኔ ኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች ዉስጥ ስለሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች፤ መለስ ዜናዊና የሙስናዋ ንግስት አዜብ መስፍን እንዲሁም ሌሎች ቱባ ቱባ ባለስልጣናት ስለሚያካሄዱት አይን ያወጣ ዘረፋ ምንም ትኩረት እንዳልሰጠ ታውቋል።

የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት UNDP ባለፈው ሳምንት ይፋ ባደረገው ሪፖርት ወያኔ ሥልጣን ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ ከ8.5 ቢሊዮን ዶላር በላይ በዘረፋ ከአገር መውጣቱ ተገልጾአል። ከዚህ በዘረፋ ወጣ ከተባለው ገንዘብ መለስ ዜናዊና ባለቤቱ አዘብ መስፍን በልጆቻቸው ሥም ጭምር ከፍተኛ መጠነ ብዙ ገንዘብ በስማቸው በተለያዩ የምዕራባዉያንና የኤሺያ ባንኮች እንዳስቀመጡ ፍንጮች እየተገኙ ነው።

### የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር/ኦብነግ/ የታገቱ የአለም የምግብ ፕሮግራም ሰራተኞችን ከእስር ማስለቀቁን ገለጸ

ኦብነግ በሚል ምህፃረ ቃል የሚታወቀው የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር በሶማሌ ክልል ጂጂጋ/ ባቢሌ አካባቢ የምትገኘዉን ጋላልሼ ከተማ ከዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ወታደሮች በማስለቀቅ ከሁለት ሳምንት በፊት ታግተዉ ወዴት እንደደረሱ ያልታወቁትን ሁለት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኞች ከእስር ማስፈታቱን ሮይተርስ የዜና ወኪል ባወጣው ዘገባ ገለፀ።

እንደ ሮይተርስ ዘገባ ኦብነግ እስረኞቹን ከማስለቀቁ በተጨማሪ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን መማረኩን የገለጸ ሲሆን ይህንኑ በተመለከተ ባወጣዉ መግለጫ ግርፋትና ሰቆቃ የደረሰባቸዉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሲቪል እስረኞችን በጋላልሼ እስር ቤት ዉስጥ አግኝቶ መፍታቱንና ከነዚህም ጋር ሁለቱን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአለም የምግብ ፕሮግራም እስረኞችን ማግኘቱን ጠቅሷል። ስለጉዳዩ ከዘረኛው አገዛዝ በኩል የተሰጠ ማረጋገጫ እንደሌለ የገለፀዉ የሮይተርስ ሪፖርት የአገዛዙ ባለስልጣኖች ቢጠየቁም እንደተለመደው " መሰረተ ቢስ ፕሮፓጋንዳ " በማለት ከማጣጣል ሊያልፉ እንዳልቻሉ አክሎ ገልጿል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአለም የምግብ ፕሮግራም ቃል አቀባይ ጁዲት ሹለር የታገቱት ሰራተኞች ስለመለቀቃቸዉ ማረጋገጫ ባይሰጡም ድርጅታቸዉ በሰራተኞቻቸዉ ላይ አደጋዉ ከደረሰ በኋላ ያቋረጠዉን የእርዳታ ተግባር በከፊል መጀመሩን ተናግረዋል።

በአካባቢዉና በደቡብ የአገሪቱ ክልሎች በሚታየዉ የድርቅ አደጋ ምክንያት 2 ሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ለረሃብ አደጋ ሊዳረጉ ስለሚችሉ የመንግስታቱ ድርጅት ባለፈዉ ወር የ75 ሚሊዮን ዶላር የምግብ ርዳታ መጠየቁ ይታወሳል።

### የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ እንደ ደርግ ዘመን ኢትዮጵያዊያን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በእለቱ ሰልፍ ላይ ከተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ጥቂቶቹን ያናገረው የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በተለይ ከአንድ ተገድዶ ከወጣ ወጣት የሚከተለዉን አስተያየት ልኮልናል- “የዘረኛውና የአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ወንበር ከተቆናጠጠበት ጊዜ ጀምሮ በሃገርና በህዝብ ሃብት እንደፈለገ ሲጨፍርና ሲዘርፍ መቆየቱ የአደባባይ ላይ ሚስጥር ሲሆን፣ አሁንም በሃያኛ አመቱ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን የሚላስ የሚቀመስ ባጡበት ወቅት ወያኔና ካድሬዎቹ በአገር አንጡራ ሃብት ለአስረሸ ምቺዉ መዘጋጀታቸዉ እጅግ የሚያሳዝን ተግባር ነዉ። ከዛሬ በኋላ እኛ ኢትዮጵያዉያን ይህንን በህዝብ ኃብት የሚደረግ ሡርግና ምላሽ ለማጥፋት ቆርጠን መነሰት አለብን” ይህንን አስተያየት የሰጠዉ ወጣት የሱን ሀሳብ የሚጋሩ ወጣቶች በሚሊዮኞች የሚቆጠሩ መሆናቸዉን ለዘገባያችብ አክሎ ገልጿል።

ይህ በዚህ እንዳለ ወያኔ የዘንድሮውን በአለ ልደቱን ያከበረው በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ሆኖ እንደነበረ ለጥበቃ ያሰማራቸው ቁጥራቸው ከሰልፈኛው ቁጥር እኩል ከነበረው ዩኒፎርም ለባሽ ወታደሮች መረዳት እንደተቻለ ዘጋቢያችን ከላከው ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ተቃውሞ ከተቀሰቀሰ ወዲያውኑ መቆጣጠር ይችላሉ ተብለው ከተመደቡት ወታደሮች በተጨማሪ የስቪል ልብስ የለበሱ የደህንነትና የፖሊስ አባላት ሰልፈኛው መሃል በብዛት ሲርመሰመሱ ከመቆየታቸው ሌላ በሰማይ ላይ የሚያንዣብቡ ሄሊኮብተሮችም ተሰማርተው ነበር።

የዘንድሮው በአል አከባበር ከወትሮው በተለየ ሁኔታ በማለዳ ተጀምሮ ከ2 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡መጠናቀቁ መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ ያሉበትን የፍርሃት ደረጃ የሚያመለክት ሲሆን ከ99 ነጥብ ስድስት በመቶ በላይ ህዝብ መርጦኛል ያለው የወያኔዉ ቁንጮ እንደለመደዉ ጥይት በማይበሳው መስታውት ውስጥ ተደብቆ አጭር ንግግር በማድረግ በአጀብ ወደመጣበት እንዳፈተለከ ታውቋል።

የወያኔን 20ኛ አመት በአል አከባበር ከአዲስ አበባ የዘገበው ቮይስ ኦፍ አሜሪካ የአማርኛው ዝግጅት ክፍል ስለበአሉ አስተያየት ከጠየቃቸው የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች የግንቦት7 ንቅናቄ ሊቀመንበር የሆኑት ዶር ብርሃኑ ነጋ አገራችን ኢትዮጵያ በረጅም ዘመን ታሪኳ ከገጠሟት ፈተናዎች ሁሉ የመለስ ዜናዊን 20 የሥልጣን አመታት ኩሉም የከፋ አድርገዉ እንደሚመለከቱት ገልጸው ከሁሉም የሚያሳዝነው የተሻለ ሥርዓት እናመጣለን ብለዉ ህይወታቸውን ለትግሉ የሰው የህወሃት አባላትን መስዋዕትነት ያረከሰ በመሆኑ ብቸኛ መፍትሄው ይህንን አስከፊ ስርዓት በተባበረ ትግል በማስወገድ ህዝብ በመረጠው መንግሥት የሚተዳደርበትን ሥርአት መፍጠር ብቻ ነው ብለዋል። የወያኔ አባላት በመሆን የመለስ ዜናዊን ጸረ አገር አጀንዳ በሃይል በማስፈጸም ላይ ያሉ ወገኖቻችንም የታገሉለት አላማ የአንድን ግለሰብ ፈልጭ ቆራጭነት ለማምጣት መሆን አለመሆኑን ቆም ብለው ማሰብና አቋማቸውን ማስተካከል እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org